## የቤጊ ወረዳ ህዝበ ውሳኔ (1987 ዓ.ም)

በሀምሌ 2 ቀን 1983 የፀደቀው የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ 2 የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ያረጋግጣል። የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ 2 መሰረት እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ እና ህዝብ የራሱን ማንነት የመጠበቅና የማስከበር ባህሉን እና ታሪኩን የማበልጸግ እንዲሁም ቋንቋውን የማሳደግ መብት አለው።

በኦሮሚያና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልሎች መካከል የይገባኛል ጥያቄ ተነስቶበት የነበረው የቤጊ ልዩ ወረዳ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ውሳኔ መሠረት ሕዝበ ውሳኔ እስከሚካሄድ ድረስ ከሁለቱም ክልሎች ውጪ በገለልተኛ አካል እንዲተዳደር መደረጉ ይታወሳል።

በመሆኑም በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ በኩል ሕዝበ ውሣኔውን ቦርዱ እንዲያስፈፅም በመጠየቁ 6 አባላት የሚገኙበት አንድ ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ቤጊ ወረዳ በመላክ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ምልመላ፣ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን አደረጃጀት እና የድምፅ ሰጪዎችን አመዘጋገብ በጥንቃቄ አጥንቶ ካስፈፀመ በኂላ ሰኔ 25 ቀን 1987 ዓ.ም. የሕዝበ ውሳኔው ድምፅ አሰጣጥ ተከናውኗል።

ለዚህ ሥራ የመራጮች ምዝገባ እና የድምፅ አሰጣጥ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የምርጫ ቅፆች፣ መዝገቦችና የሕዝበ ውሳኔ ድምፅ መስጫ ወረቀት ከማዕከል ተዘጋጅቶ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት እስከ ምርጫ ጣቢያ እንዲደርስ እና አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጓል። በጊዜው ለተነሱ አቤቱታዎች በዚያን ጊዜ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በወረዳው በሚንቀሳቀሱት የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) እና የማኦ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ማሕዴድ) አማካይነት በሕዝበ ውሳኔው አፈፃፀም ከመራጮች ምዝገባ እስከ ድምፅ አሰጣጡ ድረስ ባለው ሂደት ላይ ለኮሚቴው ቀርበው ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል።

በአጠቃላይ በ88 ቀበሌዎች ውስጥ የሚገኘው ሕዝብ ለሕዝበ ውሳኔ ድምፅ የሰጠ መሆኑን ቦርዱ አረጋግጦ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የሚከተለውን ውጤት አስተላልፏል።

| መረጃው ዓይነት | ቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|
| የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር | 56,586 | 90 % |
| ድምጽ የሰጡ መራጮች ቁጥር | 45,965 | 81.23033 % |
| ድምጽ ያልሰጡ መራጮች ቁጥር | 10,621 | 18.76966 % |
| ድምፅ የሰጠው ሕዝብ ብዛት ድምፅ መስጠት ከሚገባው ጠቅላላ ሕዝብ | | 74 % |